መዝገብ ቁጥር 23334

ሕዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንዛረፀሀይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ፍሬው ማሞ

ተጠሪ፡- 1. አቶ ደባሣ ገለታ - ቀረቡ

2. አቶ ኤባ ደመራ

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የጀመረው በምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች ባቀረበው ክስ 1ኛ ተጠሪ በሥራ ምክንያት እጁ ገብቶ የነበረውን ስንዴና የስንዴ ዱቄት ለራሱ ጥቅም ስላዋለ ግምቱን 89,750 (ሰማኒያ ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ) ይክፈል 2ኛ ተጠሪ እስከ ብር 10,000 (አሥር ሺህ ) ለሚደርስ ገንዘብ ዋስ ስለሆኑ ገንዘቡን ይክፈሉ በማለት ጠይቋል፡፡



ተጠሪዎቹ ተጠርተው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት የታየ ሲሆን ፍ/ቤቱ መዝገቡን መርምሮ ተጠሪ 16.5 ኩንታል የስንዴ ዱቄት ማጉደሉን በፊርማው ስላረጋገጠ ለመተካት ይገደዳል፡፡ 558.5 ኩንታል ስንዴ ለማጉደሉ ግን የፈረመው መተማመኛ ስለሌለ አይጠየቅም በማለት ማጉደሉ የተረጋገጠውን 16.5 ኩንታል የስንዴ ዱቄት እንዲተካ፣ 2ኛ ተጠሪ ግን ተጠያቂ አይደሉም በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ ያየው ፍ/ቤትም የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም 1ኛ ተጠሪ ለ558.5 ኩንታል ስንዴ ጉድለት ተጠያቂ አይሆንም የተባለበትን የሕግ አግባብ ለመመርምር አቤቱታው ለሰበር ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ንጠይቀው ዳኝነት የለም በማለቱ ለአቤቱታው መልስ የሰጡት 1 ብቻ ናቸው፡፡ 1ኛ ተጠሪ ነሐሴ 10 ቀን 1999 ዓ.ም በተጻፈ መልስ 558.5 ኩንታል ስንዴ የጎደለዉ በእርሳቸው ጥፋት ባልሆነ ምክንያት መሆኑን በመግለፅ ተከራክረዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው ምርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው አመልካች 1ኛ ተጠሪ 558.5 ኩንታል ስንዴ አጉድለዋል በሚል ክስ ቀርቧል፡፡ ክሱንም ለማስረዳት 1ኛ ተጠሪ የፈረሙበትን መተማመኛ አቅርቧል፡፡ በዚህ መተማመኛ 1ኛ ተጠሪ ስንዴው በጉድለት መገኘቱን አረጋግጠው ፈርመዋል፡፡ ከዚህም በላይ በዚህ ሰበር ችሎት በሰጡት መልስ ጉድለት መኖሩን አምነዋል፡፡ የስር ፍ/ቤቶች ለተገኘው ጉድለት ተጠሪ ኀላፊ አይሆኑም ያሉት በመተማመኛው ላይ ስንዴው የጎደለበት ምክንያቶች የተቀመጡና እነዚህም ጉድለቱ በተጠሪ ጥፋት የተከሰተ መሆኑን አያሳዩም በማለት ነው፡፡

እንግዲህ አመልካች 558.5 ኩንታል ስንዴ አጉድለዋል በማለት ክስ ሲመሰረት ጉድለቱ መኖሩን በቅድሚያ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ በዚህ መሠረት ጉድለቱን የሚያሳይና 1ኛ ተጠሪ የፈረሙበት መተማመኛ

አቅርቧል፡፡ ይህ ከሆነ ጉድለቱ በ1ኛ ተጠሪ ጥፋት አለመከሰቱን የማስረዳት ሸክም የማነው የሚለው ጥያቄ ይነሣል፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው በመተማመኛው ላይ ስንዴው ሊጎድል የቻለበትን ምክንያት 1ኛ ተጠሪ ዘርዝረው አስቀምጠዋል፡፡ ነገር ግን እነዚህን ምክንያቶች መዘርዘሩ ብቻ ከተጠያቂነት ሊያድናቸው አይችልም ምንም እንኳን ተጠሪው በስር ፍ/ቤት ያልተከራከሩ ቢሆንም ለሰበር አቤቱታው በሰጡት መልስ ጉድለቱን አምነዋል፡፡ ጉድለቱን አምነው በመተማመኛው ላይ ባመለከቷቸው ምክንያቶች ክሱ አይመለከተኝም የሚሉ ከሆነ ይህንኑ የማስረዳት ሸክም መወጣት እንዳለባቸው ከፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 258(1) መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ተጠርተው ባለመቅረባቸው ከሀላፊነት ነፃ የሚያደርጋቸውን የፍሬ ነገርና የሕግ ክርክር አቅርበው ክሱን አልተከላከሉም በሥር ፍ/ቤት ያልተነሣ አዲስ ነገር ደግሞ በሰበር ደረጃ ሊነሣ አይችልም፡፡

በመሆኑም ጉድለቱ መኖሩ ከተረጋገጠና ይህ ጉድለት በተጠሪው ጥፋት ያልተከሠተ መሆኑን ተጠሪው ካላስረዱ ከሀላፊነት ነፃ የሚሆኑበት ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም የጉድለቱ ምክንያቶች በመተማመኛው ላይ ተገልፀዋል በሚል ብቻ ተጠሪ ከተጠያቂነት ነፃ መሆናቸው ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል 1ኛ ተጠሪ አጎደሉ ለተባሉት የስንዴ ዱቄትና ስንዴ በክሱ ላይ የተመለከተውን ዋጋ ተቃውመው ያቀረቡት ክርክር ሳይኖር የሥር ፍ/ቤቶች የአንድ ኩንታል የስንዴ ዱቄት ዋጋ አልተገለፀም በሚል 1ኛ ተጠሪ የስንዴ ዱቄቱን በአይነት እንዲመልሱ የሠጡት ውሳኔ አግባብ አይደለም፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1) የምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የመ/ቁ00468 በጥር 25 ቀን 1996 ዓ.ም እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 07116 በታህሳስ 11 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡

2) 1ኛ ተጠሪ ለጎደለው 16.5 ኩንታል የስንዴ ዱቄት እና 558.5 ኩንታል ስንዴ ተጠያቂ ስለሆኑ ክስ የቀረበበትን 89,750.50 (ሰማንያ ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሃምሣ ብር ከሃምሳ ሣንቲም) ይክፈሉ፡፡ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ ሕጋዊ ወለድ ጨምረው ይክፈሉ፡፡

3) ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 25899

ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ
መስፍን ዕቁበዮናስ
መድኅን ኪሮስ
ዓሊ መሐመድ
ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- የማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ተስፋዬ ምንዳገኝ ቀረቡ።

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ስዩም ካሣ - አልቀረቡም።

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የጀመረው በኦ/ብ/ክ/መ/ የአሩሲ ዞን ከ/ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች በተጠሪው ላይ ሰኔ 11 ቀን 1994 ዓ.ም. ባቀረበው ክስ ሲሆን ይዘቱም ተጠሪው ጡረታ ወጥተው ጡረታ አበል እየተከፈላቸው ከሕግ ውጪ በመንግሥት መ/ቤት /የአሠላ ማዚጋጃ ቤት/ ተቀጥረው ደሞዝም እያገኙ በመሆኑ ከሰኔ 1 ቀን 1987 ዓ.ም. እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1988 ዓ.ም.